# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 7: «በቀና አናግሬት»

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: AT BONGO ACADEMY**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE 2: ምኞቴ AT HIS MOTHER'S PLACE**

- **ወ/ሮ የውድዳር (F, 60)**
- **ምኞቴ (M, 35)**

**SCENE 3: AT THE PRINCIPAL'S OFFICE**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**SCENE 4: አቶ መኩሪያ BRIBES THE POLICE**

- **ፖሊስ ሙሉጌታ (M, 45)**
- **አቶ መኩሪያ (M, 45)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

**ጤና ይስጥልን የበማድመጥ መማር ድራማ ተከታታዮች፤ ይህ «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ– «መዘዙን መቀበል» የተሰኘው ድራማ ሁለተኛ ዙር ክፍል 7 ዝግጅት ነው ።እስቲ ባለፈዉ ያቆምንበትን መለስ ብለን እንቃኝ። … የ15 አመቷ ትዕግስት ከቀድሞ ፍቅረኛዋ እና የታክሲ ረዳቱ ምኞቴ የሚደንቅ ሀሳብ ቀርቦላት ነበር።**

## 2. EPISODE 2, LINES 60 – 64:

*ምኞቴ: (…)ከእንግዲህ አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ?*

***SFX: BOOKS FALLING DOWN***

*ትዕግስት: ምን?*

*ምኞቴ: አፈቅርሻለሁ ትዕግስት*

*ትዕግስት: ምኞቴ… እኔ… እኔ አላውቅም።*

## 3. NARRATOR:

**የትዕግስት የክፍል ጎደኞች በእርግጥ በአዕምሮዋቸው በርካታ ነገሮች ይመላለሱባቸዋል። ንጉሴን ብንመለከት ከልቡ የሚወዳት ምህረት እንደማትፈልገው ከነገረችው ጀምሮ እውነታውን መቀበል አቅቶታል። ባለፈው ክፍል ወላጆቹ ጎዳና ላይ ጥንብዝ ብሎ ሰክሮ ነበር ያገኙት።**

ይህ በእንዲህ እንዳለ የምህረት አባት አቶ ሙላቱ በተጠረጠሩበት የስርቆት ወንጀል ታስረው ፖሊስ ጣቢያ ነው የሚገኙት። በእርግጥ ወንጀሉን ፈፅመው ይሆን? ለዚህ ዛሬ መልሱን እናገኛለን። …

የአቶ ሙላቱ ልጅ ምህረት ፈፅሞ የተለየ ችግር ገጥሟታል። ከክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል አርግዛለች። እሱ ግን ኃላፊነት መውሰድ አይፈልግም። እንደውም ምህረት በጭካኔ ፅንሱን እንድታስወርድ ነው የነገራት፤ በእርግጥ ባያሳምናትም ማለት ነው። የዳኒ ጓደኛ በለጠ በበኩሉ የተወሰኑ ምክሮችን ለግሶታል።:

## 4. EPISODE 5, LINE 109:

***BIKO:*** *(…)አንዳንዴ ሴቶች ከኛ የሚፈልጉት በቀናእንድናናግራቸው ነው።*

## 5. NARRATOR:

የዛሬው ጭውውት ርዕስም ይኸው ነው «በቀና አናግራት» ይሰኛል። የምንጀምረው ዳንኤል፣ ምህረት እና ሌሎቹ ወጣቶች ከሚማሩበት የቦንጎ አካዴሚ ይሆናል። …

## <u>SCENE 1: AT BONGO ACADEMY</u>

## 6. SFX: BONGO ACADEMY CLASSROOM, INTERIOR ATMO

## 7. SFX: SCHOOL BELL RINGS

**8.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እሺ ተማሪዎች የዛሬው ትምህርት እዚህ ላይ ይጠናቀቃል። ነገ እንገናኛለን። ወረቀታችሁን ክፍል ከመጀመሩ በፊት እንድታስረክቡ።ንጉሴ: ደግሞ ከ15 ደቂቃ በኋላ ቢሮዬ እንድትመጣ።

**9. SFX: DOOR OPENING, HIGH-HEELED FOOTSTEPS LEAVING (ርዕሰ መምህርት ሰብለ)**

**10. SFX: NOISE AS CLASS PACKS AND DISPERSES**

**11.** ዳንኤል: ታድያስ ምህረት እንዴት ነሽ?

**12.** ምህረት: ምን ፈለክ ዳንኤል? ሰላሜን ስጠኝ እሺ?

***KW BEGIN***

**13.** ዳንኤል: ኧረ ባክሽ ምህረት ማውራት አለብን።

**14.** ምህረት: **(angry)** ነው እንዴ!! አሁን ማውራት ፈለክ ዳንኤል? አጠገብህ እንዳልደርስ የነገርከኝ መስሎኝ እኮ ነበር!

**15.** ዳንኤል: **(trying to keep it down)** ኧረ በናትሽ አብደዛ  አትጩሂ። አንዴ ብቻችንን ልንነጋገር እንችላለን?

**16.** ምህረት: ኧረ ባክህ!  አንዴ ለብቻችን? ትቀልዳለህ ልበል? ።በል ይልቅ ተማሪው በሙሉ ከክፍል ወጥቷል፤ አንተም ብትሄድ ይሻልሃል።

**17.** ዳንኤል: **(sudden change of tone, sweetly)** ተመልሰን አብረን እንድንሆን እፈልጋለሁ ምህረት። ናፍቀሽኛል።

**18.** ምህረት: **(flatly)** አቁም ዳንኤል። ያንተ ጨዋታ ሰልችቶኛል።ከእንግዲህ እንድትጎዳኝም አልፈልግም። በቅቶኛል።

**19.** ዳንኤል: **(trying to convince her)** ይገባኛል ምህረት። ለዛ ስትይ አንዴ የምልሽን አስጨርሺኝ።

**20.** ምህረት: አምስት ደቂቃ ብቻ ነው መቆየት የምችለው። እናቴ በእኔ ላይ ድንገት ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግ ጀምራለች። የሆነ ነገር ሳትጠረጥር አልቀረችም። እሺ ምንድን ነው ልትነግረኝ የፈለከው?

***KW END***

**21.** ዳንኤል: ምህረት አፈቅርሻለሁ…

**22.** ምህረት: **(loudly)** ዳንኤል ላንተ ማፍቀር ማለት እንዲህ ነው? እየተጠቀምክብኝ ከዛ ደግሞ እንደ ቆሻሻ እየጣልክ እና እያበሻቀጥከኝ?

**23.** ዳንኤል: ምህረት ግራ ተጋብቼ ነበር።

**24.** ምህረት: ስታስረግዘኝ ግን ግራ ተጋብተህ የነበረ አይመስለኝም። በፍቅሬ እንዳበድክ ስትነግረኝም ግራ ተጋብተህ የነበረ አይመስለኝምነበር። ወይንም ደግሞ ገንዘቡን እንዲያ ጎዳና ላይ የወረወርክልኝ ጊዜ። እኔ ለአንተ ምንም እንደሆንኩ በጣም በጣም ግልፅ አድርገህልኛል።

**25.** ዳንኤል: ይቅርታ አርጊልኝ።

**26.** ምህረት: ይቅርታ? ለዛ አሁን ጊዜው ረፍዷል። አርግዤያለሁ ዳንኤል -**(breaks down)** እርጉዝ ነኝ ሆኖም ብቻዬን እወጣዋለሁ በቃልክ አብረን ያላደረግነው ይመስል፤ አይደል።

**27.** ዳንኤል: አባክሽን አታልቅሺ።

**28.** ምህረት: **(sniffles)**

**29.** ዳንኤል: ተመልሰን አብረን እንድንሆን እፈልጋለሁ። ግን ፅንሱን ማስወረድ አለብሽ ምህረት።

**30.** ምህረት: አሀ! እሄ ሁላ ለዚህ ነው እንዴ? ፅንሱን እንዳቋ -- **(stops in horror as footsteps approach)**

**31. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS APPROACHING**

**32.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምኑ ነው የሚያቋርጠው ምህረት? ምንድን ነው እየተከናወነ ያለው?

**33. SILENCE**

**34.** ዳንኤል: **(scared)** እትዬ … እእ … መምህርት … ርዕሰ መምህርት ሰብለ…

**35.** ምህረት: **(pulling herself together)** ወረቀቱን። ዳንኤል ሊረዳኝ እንደሚፈልግ እየነገረኝ ነበር። እኔ ግን ብቻዬን ብሰራው እመርጣለሁ።

**36.** ዳንኤል: **(in relief)** አዎ! ወረቀቱ! እኔማ በጋራ ብንሰራ ጠቃሚ ነው ብዬ አስቤ ነበር።

**37.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(stern)** ዳንኤል አንተ በጋራ መስራት የምትለው እኛ አስተማሪዎች ማታለል የምንለውን ነው። ምንም የጋራ ስራ ብሎ ነገር የለም። **(to** ምህረት**)** ምህረት ደህና አይደለሽም እንዴ?

**38.** ምህረት: **(still sniffling)** ደህና ነኝ። አመሰግናለሁ ርዕሰ መምህርት። ትንሽ ጉንፋን ሊይዘኝ ነው መሰለኝ።

**39.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(not convinced)** እእእ … ነው እንዴ ። በሉ እስከ ነገ። ሁለት የተለያዩ ወረቀቶች ማየት እፈልጋለሁ። ግልፅ ነው?

**40.** ዳንኤል/ምህረት: አዎን ርዕሰ መምህርት ሰብለ።

**41.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(to herself)** አሁን እንደው ማስታወሻዬን የት ይሆን የረሳሁት?

**(fade out as we follow ዳንኤል and ምህረት)**

**42. SFX: FOOTSTEPS OF ዳንኤል AND ምህረት IN THE HALLWAY**

**43.** ዳንኤል: **(they whisper)** ወይኔ! ለጥቂት! እንኳንም ስለዛ ስናወራ አልሰማችን። ታውቂያለሽ--

**44.** ምህረት: ከእንግዲህ ስለእዛ ጉዳይ ትምህርት ቤት ውስጥ ማውራት አልፈልግም።

**45.** ዳንኤል: ምህረትዬ እንዴት እንደምጨነቅልሽ እኮ። በእዚህ የተነሳ ትምህርትሽን እንድታቋርጪ አልፈልግም።

**46. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**47.** ምህረት: **(realizes)** ርዕሰ መምህርት ሰብለን ፈርተህ ነው!

**48.** ዳንኤል: ኧረ ባክሽ! ይሄ እንኳን እውነት አይደለም። ላንቺ ጥሩውን ብቻ ስለምፈልግ ነው።

**49.** ምህረት: ዳኒ --

**50.** ዳንኤል: ለገንዘቡ ብለሽ ከሆነ --

**51.** ምህረት: **(cuts in decisively)** ዳንኤል ተወው በቃ! እኔን እንደእዛ ብሽቅጥቅጥ ያደረከኝ አንዴ ብቻ ነው ግን በዛው መጠን ዕድልህን አበላሽተሃል። አሁን መሄድ አለብኝ።

**52. SFX: FOOTSTEPS AS ምህረት LEAVES**

**53.** ዳንኤል: ምህረት ቆይ! እና አሁን…እንትን ትይዋለሽ ወይንስ አትይውም?

**54.** ምህረት: **(calls back)** ያ ከአሁን በኋላ ያንተ ጉዳይ አይደለም። ዳንኤል!

**55.** ዳንኤል: **(to himself)** ብሽቅ! እንደእዛ ጥሩ ሆኜ ስላናገርኳት ብቻ… በለጠ ለእዛ ጠቃሚ ምክርህ ከልብ አመሰግናለሁ!

**56. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: ምኞቴ AT HIS MOTHER’S PLACE</u>**

**57. ATMO: RURAL BACKGROUND**

**58. SFX: STEPS APPROACHING ON GRASS**

**59.** ወ/ሮ የውድዳር: **(sickly)** የኔው ጉድ፤ አንተ እንዳትሆን ብቻ። ምኞቴ?

**60.** ምኞቴ: አዎ! ነኝ እንዴት ነሽ እማ ተሻለሽ?

**61.** ወ/ሮ የውድዳር: እዚህ ቤት ውስጥ ውር ውር እያሉ የሚቦርቁ የልጅ ልጆች ቢኖሩኝ ኖር በደስታ እሞት ነበር።

**62.** ምኞቴ: እማዬ! አትሞቺም። እንዲህ ስትይ ብዙ አመታት ተቆጠሩ።

***KW BEGIN***

**63.** ወ/ሮ የውድዳር: ልጄ አንተ የምልህ አይገባህም። ይህንን የተዳከመ የጃጀ ማንነቴን ለአንድ ቀን ባውስህና ብታየው ምናልባት የዛን ጊዜ የምህል ይገባህ ይሆናል። እባክህ እስኪ እዛጋ ካለው ሻይ ትንሽ አዳልኝ።

**64. SFX: TEA BEING POURED INTO CUP,** ወ/ሮ የውድዳር **DRINKING**

**65.** ወ/ሮ የውድዳር: እሺ ምኞቴ። በል እስኪ ንገረኝ። መቼ ነው የምታገባውና የልጅ ልጆች የማየው በል?

**66.** ምኞቴ: አይንሽ ታውሯል። እማዬ ምኑን አየሽው።

**67.** ወ/ሮ የውድዳር: እሰይ! ሹል ምላስማ እንዲህ ከአፍህ መች ጠፍቶያውቅና ። አዩ ብታውቀውማ የኔ አይነ ስውርነት፤ ወጣትነት ቀስ እያለ ደብዛቸ ጠፊ መሆኑን ባስታወሰህ ነበር።

**68.** ምኞቴ: የሚቀመስ ነገር አገኘሽ?

***KW END***

**69.** ወ/ሮ የውድዳር: የምልህን ትሰማለህ ምኞቴ? ፍጠን የልጅ ልጄን አምጣልኝ።

**70. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 3: AT THE PRINCIPAL’S OFFICE

**71. ATMO: INTERIOR ATMO, BONGO ACADEMY, DAYTIME, AFTER SCHOOL.**

**72.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ንጉሴ እንደምን አለህ?

**73.** ንጉሴ: ምንም አልል። አመሰግናለሁ ርዕሰ መምህርት ሰብለ።

**74.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ወላጆችህስ እንዴት ናቸው?

**75.** ንጉሴ: እነሱም ምንም አይሉ። ለምን ጠየቁኝ?

**76. SFX: PAPERS BEING SHUFFLED**

**77.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ወጤትህ እየቀነሰ መጥቷል። ክፍል ውስጥም በጥሞና አትከታተልም። በዛ ላይ የተወሰኑ ጊዜያት የቤት ስራህን ሳትሰራ ይዤህለሁ ፤ንጉሴ። በአንተ ላይ ያለን ተስፋ ትልቅ ነው። ለወትሮው ከጎበዝ ተማሪዎች ሁሉ ተርታ ነበር ምድብህ። ምንድን ነው የሆንከው?

**78.** ንጉሴ: **(trying to sound convincing)** ምንም እኔ… እኔ… በአሁኑ ሰዓት በሁሉም የትምህርት አይነቶች ብዙ የቤት ስራዎች ስላሉን ነው።

**79.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ይገባኛል። ግን - በርትተህ ስራ እሺ?

**80.** ንጉሴ: እሺ ርዕሰ መምህርት ሰብለ

**81.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እባክህን አስተውል። እንደ ክፍል አለቃነትህ ለሌሎቹ ተማሪዎች አርአያ መሆን አለብህ። ካለበዚያ የክፍል አለቅነቱን ለሌላ ተማሪ መስጠቴ ነው።

**82.** ንጉሴ: እሺ። ርዕሰ መምህርት ሰብለ። ድጋሚ አያዝኑብኝም። ቃል እገባልዎታለሁ።

**83.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: በል እሺ አሁን መሄድ ትችላለህ።

**84. SFX: FOOTSTEPS ንጉሴ LEAVES**

***KW BEGIN***

**85.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ቆይማ - ንጉሴ አንድ ነገር። እንደ ክፍል አለቃነትህ አክፍል ውስጥ ለሚሆነው ነገር አይንንና ጆሯችን ነህ። በምህረት እና ዳንኤል መካከል ምን እየሆነ ነው ያለው?

**86.** ንጉሴ: **(from the door)** እ… እኔንጃ ርዕሰ መምህርት

**87.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ጥሩ። በል እሺ ደህና ሁን ንጉሴ

**88.** ንጉሴ: ደህና ይሁኑ።

***KW END***

**89. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**90. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: አቶ መኩሪያ BRIBING THE POLICE</u>**

**91. ATMO: EVENING SOUNDS IN A QIUET ENVIRONMENT, CRICKETS**

**92. SFX: OFFICER’S FOOTSTEPS ON GRAVEL**

***KW BEGIN***

**93. SFX: CELLPHONE RINGS, CALL ANSWERED**

**94.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ሄሎ ፖሊስ ሙሉጌታ ነኝ!

**95.** አቶ መኩሪያ: **(on phone)** ሄሎ ፖሊስ ፤መኩሪያ ነኝ።

**96.** ፖሊስ ሙሉጌታ: ምኑጋ ነህ?

**97.** አቶ መኩሪያ: የተለመደው ቦታ መኪናዬን አቁሜያለሁ።

**98.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እሺ መጣሁ።

**99. SFX: PHONE CALL DISCONNECTED**

***KW END***

**100. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**101. SFX: CAR WINDOW ROLLING DOWN AUTOMATICALLY**

**102.** አቶ መኩሪያ: **(low voice)** ሰላም! ፖሊስ ሙሉጌታ። ማንም እንዳልተከተለህ እርግዘኛ ነህ?

**103.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(offended)** የተከበሩ የምክር ቤት አባል አቶ መኩሪያ። ፖሊስ እኮ ነኝ። ሰው ተከትሎኝ ቢሆን ኖሮ አውቅ ነበር።

**104. SFX: BILLS BEING COUNTED AND HANDED OVER**

**105.** አቶ መኩሪያ: ይሄውልህ ገንዘቡ። በል ሙላቱ አድሜ ልኩን ከእስር ቤት እንዳይወጣ አድርግልኝ። ማንም እንደማይደርስበት አድርጌ ከስርቆት ወንጀሉ ጋ አነካክቸዋለሁ።

**106.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(low voice)** ይህ በቂ አይደለም። ያለ ማስረጃ በስርቆት ወንጀል ማቆየቱን ከባድ ያደርገዋል። አሁን ደግሞ ነገሮች ሁሉ ከባድ እየሆኑ መጥተዋል።ባለቤቱ ሉሊት በየቀኑ ፖሊስ ጣቢያ እየተመላለሰች ነው። ስለልጇ መጠየቋን አላቋረጠችም። ከባዱ ስለገዛኸው ልጅ። ...

**107.** አቶ መኩሪያ: ስማኝ ፖሊስ። ገንዘብ አይደለም ችግሩ። ገንዘቡ የሚመጣበት በርካታ መንገዶች አሉ።አንተ ብቻ ድርሻህን በአግባቡ ፈፅም።

**108.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እንደዛ ከሆነ የተከበሩ የምክር ቤት አባል በእኔ ይሁንቦት አቶ ሙላቱ ለረዥም ጊዜ እስር ቤቷን እንደማይለቅ ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ። እርስዎ ብቻ እኛ እንዳንራብ ያድርጉ። የምልዎ ከገባዎ! **(laughs)**

**109.** አቶ መኩሪያ: የባለቤቱስ ጉዳይ? ልጇን እያለች መጮኺን ብትቀጥልስ?

**110.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እሱን ለኔ ይተውት። እሷ ማወቅ የሚገባት ነገር ቢኖር ጉዳዩን እየተከታተልን መሆኑን ነው። እዚህ ሀገር ደግሞ እንዲህ አይነት ነገር አመታት ሊፈጅ ይችላል።**(laughs sarcastically)** ልጇ ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ጋ እንደሆነች ነግሬያታለሁ።

**111.** አቶ መኩሪያ: **(laughs)** የኔ ቤት በአሁኑ ጊዜ እንዲህ ተብሎ የሚጠራ ከሆነ ጥሩ!...ለማንኛው እኔ የፖለቲካ አባል መሆኔን አትዘንጋ፤ ስለዚህ ጉዳይ ለመገናኛ ብዙሃን የሚሆን አንዳች ክፍተት እንዳይፈጠር አደራ።። መቼም ስሜ ያለአግባብየመጀመሪያ ገፅ ላይ ሰፍሮ ማየቱን አንፈልግም። !

**112. SFX: ELECTRIC CAR WINDOW CLOSING**

**113. SFX: CAR DRIVES OFF**

**114. SFX: STEPS AS OFFICER LEAVES**

**115.** ፖሊስ ሙሉጌታ: **(whistling/humming happily)**

**116. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

እንግዲህ ለዛሬ ያልነው የአስካሁኑ ነበር። ለመሆኑ አቶ መኩሪያ እና ሙሰኛው ፖሊስ ይህንን ጉዳይ በምስጢር ይዘው ማቆየቱ ይሳካላቸው ይሆን? ምህረት፣ ዳንኤል፣ ንጉሴ እና ትዕግስትስ ምን የሚጠብቃቸው ይመስላችኋል? ይህንን ለማወቅ እስከሚቀጥለው የጭውውት ጊዜ መጠበቅ ሊኖርባችሁ ነው። እስከዛው መጠበቅ ካቃታችሁ ግን በቀጥታ dw.de/lbe ድረ ገፅ ላይ እንድትገቡ እንጋብዛለን። እዛም «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» ድራማን የሚመለከቱ አዳዲስ ክንዋኔዎችን ታገኛላችሁ። በተለይ ላቦሪያ በሚባለው የዳንኤል አገር ውስጥ ነዋሪ በሆነችው ና አልማዝ በምትባለው ልጅ የተቀረፀውን የቪዲዮ ዘገባ ማንም ሳይቀድማችሁ ነው የምታገኙት። በነገራችን ላይ ልጅቷ ማን እንደሆነች ልንገራችሁ? ዝም ብላ ልጅ እንዳትመስላችሁ፤ ማን መሰለቻችሁ? አይ! እንደውም ይቅር ዝርዝር ነገሩንማ ... አልንገራችሁም። በራሳችሁ ጊዜ ልትደርሱበት ይገባል! ። እንግዲህ በፌስ ቡክ ገፃችን ላይም መወያየታችሁን አትርሱ። ጤና ይስጥልን።